# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 219 ሐምሌ 19 2004 ገጽ 1


**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል። በጠላት ካምፕ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን እንዲቀላቀሉን ጥሪ ያደርጋል።**

**ግንቦት 7 መተማመኛችን ኅብረታች እና የገዛ ራሳችን ተነሳሽነት ነው ብሎ ያምናል። ሁላችንም ታጋዮች፣ ሁላችንም አርበኖች፣ ሁላችንም ዲፕሎማቶች እና ሁላችንም ጋዜጠኞች እንሁን።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጥምረትና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸዉን የጋራ መግለጫ በማዉጣት ገለጹ

በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራዉ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርና ጥምረት ለነፃነት፤ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ ዘረኛዉን የመለስ ዜናዊ ስርዐት ለማስወገድ የሚደረገዉን ማንኛዉንም አይነት ትግል በጋራ ለማካሄድ ከስምምነት ላይ መድረሳቸዉን ሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓም ባወጡት የጋራ መግለጫ ለህዝብ ይፋ አደረጉ።

ጥምረትና ኦነግ በዚህ በያዝነዉ ሳምንት መጀመሪያ ላይ በድረ ገፆቻቸዉና በተለያዩ የኢትዮጵያ ድረ ገፆች በለጠፉት በዚህ መግለጫቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት የጠየቀዉ የትብብር ጥያቄ ምላሽ ማግኘት እንዳለበትና ይህ የተቃዋሚ ድርጅቶች ህብረትና ትብብር ላለፉት ሃያ አንድ አመታት የኢትዮጵያን ህዝብ በግፍ የገዛዉንና የረገጠዉን ዘረኛ የወያኔ ስርዐት ማስወገድ እንደሚገባዉ ግልጽ አድረገዋል።

እነዚህ ሁለት የትግል አጋር ድርጅቶች ሰፋ ያለና ሁሉንም የኢትዮጵያ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ያቀፈ የገራ ግንባር እንዲፈጠር ለሁሉም ድርጅቶች ጥሪ አቅርበዋል። ሆኖም ይህ ሰፋ ያለ ግንባር እስኪፈጠር ድረስ እነሱ በተቀናጀ መልኩ የሚያካሄዱት ትግል የሚቀጥል መሆኑን በመግለጫቸዉ ላይ አክለዉ ገልጸዋል።

ጥምረትና ኦነግ ዘረኛዉን የወያኔ ስርአት ለማስወገድና ከዚህ ስርአት መወገድ በሁዋላ የሚኖረዉን የሽግግር ግዜ በተመለከተ ሁሉን አቀፍ ዲሚክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት የሚያስችሉ ምሰሶዎች ናቸዉ ብለዉ ባመኑባቸዉ በሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ሙሉ በሙሉ መስማማታቸዉን በጋራ መግለጫቸዉ አሳዉቀዋል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ጥምረትና ኦነግን በጋራ ያወጡትን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 3 ያንብቡ

## ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አሁንም ከማገገሚያ ክፍል እንዳልወጣ ምንጮች ገለጹ

ቤልጂዬም ብራሰል በሚገኘው የሴይንት ሉክ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ውስጥ ህይወታቸው አደጋ ላይ የወደቁ ሰዎች የመተንፈሻና የፈሳሽ ምግብ ቱቦዎ ተገጥሞላቸው በሚተኙበት የሪከቨሪ ሩም እየተባለ በሚጠራው የህክምና ክፍል ውስጥ እንደሚገኝ ከሆስፒታል ምንጮች ያገኘነው መረጃ አረጋገጠ።

መለስ ዜናዊ እራሱን ስቶ በቻርተር አውሮፕላን ወደ ቤልጂዬም ከተላከ ወዲህ ላለፉት 3 ሳምንታት እራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የገለጹ ምንጮች ከአሁን አሁን ይሞታል ተብሎ ሲጠበቅ ነፍሱ መለስ እንደሚልና ተሽሎታል ተብሎ ሲታሰብ ደግሞ ወዲያውኑ መልሶ እንደሚወስደው አረጋግጠዋል።

የመለስ ዜናዊን ህመም በቅርበት ሆኖ እያስታመመ ያለው የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ዴታ ተብሎ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በታኮነት ከመመደቡ በፊት በዩናይትድ ስቴትስና በቤልጂዬም የወያኔ አምባሳደር በመሆን ለ19 አመት ያገለገለው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ መሆኑ ተረጋግጧል።

የግንቦት 7 መረጃና ክትትል ጓዶች ባካሄዱት ስውር ክትትል ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ዘወትር ጠዋት በአንድ አፍሪካዊ በሚሽከረከር የኮር ዲፕሎማቲክ መኪና መለስ ዜናዊ ብራሰልስ ውስጥ ወደተኛበት ሆስፒታል እንደሚመላለስ ለማረጋገጥ ተችሎአል። መለስ ዜናዊ ሆስፒታል ከገባበት ቀን ጀምሮ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ለአንድም ቀን በአስታማሚነት ከጎኑ ተለይቶ እንደማያውቅ ተደርሶበታል። በአንጻሩ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን የብርሃኔ ገብረክርስቶስን ግማሽ ካባለቤቷ ጋር ለመቆየት አለመፈለጓ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉትን ሁሉ ያስገረመ ሆኗል ተብሏል።

ይህ በዚህ እዳለ በወያኔ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ሚዲያዎቻና አፍቃሪዎቻቸው አለቃቸው መለስ ዜናዊ በዕረፍት ላይ እንደሆነ አስመስለው የሚያሰራጩትን ዜና አጠናክረው እንደቀጠሉበት ለማወቅ ተችሎአል። በትናንትናው ዕለት የታተመው ሪፖርተር ጋዜጣ "ጠቅላይ ሚንስቴር መለስ ዜናዊ ከሐኪሞቻቸው ባገኙት ምክር መሠረት በውጭ አገር በዕረፍት ላይ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግዜ

### የሰሞኑ የወያኔ ባለስልጣናት ግሽበት ሃምሳ በመቶ ቀንሷል ዜማ በዓለም ታይቶና ተሰምቶ የማያቅ አሳሳች የቁጥር ጨዋታ ቅጥፈት መሆኑን አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ገለጸ

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ግሽበት በቁጥር ጨዋታና በሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሚሸፈንበት ደረጃ ልቆ በመሄድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በማንሳት እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር ይሻላል ሲል አንዳችም እውነት ተናግሮ ለማያውቀው ወያኔ ምክር ለመለገስ ሞክሯል።

ጋዜጣው በማያያዝም አንዴ የግሽበቱ ምክንያት ስግብግብ ነጋዴዎች ናቸው ሲባል፣ ሌላ ጊዜ ግሽበቱ ከውጭ የመጣ ነው እየተባለ አሳሳች ምክንያቶች ሲደረደሩ በቋሚ ገቢ የሚተዳደረው፣ ጡረተውኛና በድኅማ የሚኖረው ዜጋ ኑሮን መኖር እየተወ መጥቷል:: ከዋጋ ንረቱ ጋር ፉክክር ይዘው በአሸናፊነት በመወጣት በተንደላቀቀ ድግስና ፈንጠዚያ ታጅበው የሚኖሩና እንዲኖሩ የተደረጉ ጥቂት ደልቃቆች ቢኖሩም፣ አብዛኛው ሕዝብ የኑሮ ውድነት ክብደቱ ‹‹ከጭነት ልክ በላይ›› ሆኖበታል በማለት አብራርቷል::

የግሽበቱን መሰረታዊ ምክንያት በጥናት ከማረጋገጥ፣ ወይም በሙያው እውቀት ያላቸው ዜጎች የሚያስረዱትን ከማዳመጥ ይልቅ በአሳሳች ስታትስቲክሶች ለመሸፋፈን መሞከሩ፣ የተሞከረውንም መፍትሄ እንዳይሰራ አድርጎታል ያለው ጋዜጣው ይኸውም ይላል መፍትሄው ስንዴ ከውጭ አስመጥቶ ማከፋፈል ነው ተባለ፣ ስንዴው መጣ ተከፋፈለ፣ ግሽበት ግን ማሻቀቡን ቀጠለ፤ ሳቢያውም እውነተኛውን ምክንያት ለማወቅ አለመፈለግ ነው ብሏል።

በማከልም ሰሞኑን ደግሞ ‹‹የዋጋ ግሽበት ቀነሰ›› እየተባለ በስፋትና በተደጋጋሚ እየተነገረ ነው:: የንግግሮች ሁሉ ‹‹አዝማች›› ሆኗል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### በኢትዮጵያ ከሁሉም አቅጣጫ በሚሰነዘርበት ተቃውሞ እየተደናገጠ የመጣው የወያኔ ስርዓት ሰሞኑን በቃሊቲ ወህኒ ቤት ጥብቅ ፍተሻ ማካሄዱ ተሰማ

ከአካባቢው የተገኙ መረጃዎች እንዳመለከቱት በተለይ የሰሞኑ የሙስሊሞች ሰላማዊ የመብታችን ይከበር ጥያቄ አጠቃላዩን የዜጎች የነጻነት ጥያቄ መንፈስ ማነሳሳት ወደ ወህኒ ቤቱም ዘልቋል በሚል ጭንቀት እሁድ ሀምሌ 25 ቀን 2004 ዓ.ም ነው በወህኒ ቤቱ አጠቃላይ ፍተሻ የተካሄደው።

እንደ ምንጮቹ እስረኞቹ አንድ በአንድ የሰውነት አካላቸውና ማደሪያ አካባቢያቸው የተፈተሸ ሲሆን የተገኙ ጥፍር መቁረጫዎች ሳይቀሩ ተወስደዋል። በግቢው ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮችም ተለቅመው ተጥለዋል።

በዚሁ ጉዳይ ላይ የዘገበው ፍኖተ ነጻነት እንደገለጸው ደግሞ በተለይ በሴቶች ማደሪያ በተደረገው ፍተሻ ለመክተፊያ የሚጠቀሙባቸው ቆርቆሮዎችና ታኮ ጫማዎች ጭምር ተወስደውባቸዋል።

የወያኔ መንግስት በቁጥጥሩ ስር ያሉትን እስረኞች እንኳን እንዲህ መፍራቱ ስርዓቱ በአሁኑ ወቅት የሚይዘው የሚጨብጠው እንደጠፋውና የውድቀቱ ዋዜማ ላይ መድረሱን የሚያመላክት ነው ሲሉ ምንጮቹ ገልጸዋል።

### የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ለሐይማኖት ነፃነትና ለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚያደርጉት ትግል ወደ ከፍተኛ ምዕራፍ ተሸጋጋረ

ለወራት የዘለቀዉና የአምልኮ መብታችን ይክበር የመንግስት ጣልቃ ገብነት ይቁም የሚለዉ የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች የመብትና የነፃነት ጥያቄ አሁንም እንደቀጠለ ነዉ። አገዛዙ ጡንቻዉን ተማምኖ "ጆሮ ዳባ ልበስ" ብሏል ህዝብ ሙስሊሙ ግን ትግሉን አጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ከአዲስ አበባ የሚደርሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ።

ባሳለፍነዉ ሳምንት መገባደጃ አርብና ቅዳሜ የኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ በሠላማዊ ሠልፈኞችና ሠልፉን ለመበተን በወጣዉ የወያኔ ታጣቂ ሀይል መካከል በየመስጊዱና በየአደባባዩ በተካሄደዉ ግብግብ ስትተራመስ መዋሏን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከሥፍራው በላከልን ዘገባ ገልጾአል።

እንደ ሪፖርተራችን ዘገባ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላዉ ህዝብ የተሳተፈበትና አርብ ሐምሌ 13 ቀን የተካሄደዉ ሠላማዊ ሠልፍ ምንም አይነት እንከን ሳይገጥመዉ በሰላም ተጀምሮ በሠላም ተፈጽሟል። በዚህ ቁጥሩ ከ500 ሺ በላይ የሚሆን ሠላማዊ ሰልፈኛ በተገኘበት ሠልፍ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የድል መዳረሻ ላይ ነን፤ ትግሉን ተቀላቀሉ!!!

ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የምናደርገው ትግል ወደ ድል ተዳርሷል። ትግላችን ከእስልምና ወይም ክርስትና አድማስ ወጥቶ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ትግል እየሆነ ነው። መስጊዶች የትግል ማዕከል እንደሆኑ ሁሉ ቤተክርስያኖችም በተመሳሳይ የትግል ማዕከል ይሆናሉ። በአመቸን ቦታ ሁሉ ተቃውሞዓችን እናሰማለን። የተንገዳገደው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ጨርሶ እስኪወድቅ ድረስ በየእለቱ ትግላችንን እያጠነከርን እንሄዳለን። ወደ ድላችን መዳረሻ ላይ እንገኛለን፤ ተቀላቀሉን።

የትግላችን አጨራረስ የግብጽን ይምሰል ወይም የሊቢያ ለጊዜው የለየለት አይመስልም። እኛ ግን ለሁለቱም ተዘጋጅተናል።

ባለፈው ዓርብ የሮመዳን ወር የመጀመሪያው ቀን በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ አካባቢ ተገኝቶ በሚያስገርም ድርጅታዊ ብቃት ተቃውሞውን በፀጥታ የገለፀው ሰው ብዛት በግብጽ ታህሪር አደባባይ ከነበረው የሚተናነስ አልነበረም። እርግጥ ነው የኢትዮጵያዊያኑ ተቃውሞ የግብጹን አንድ መቶኛ ያህል እንኳን የሚዲያ ትኩረት አልሳበም። በብዛት አኳያ ሲታይ ግን በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛ ምሥራቅ ከታዩት ሕዝባዊ አመጾች ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል። ይህ እጅግ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው። በሚቀጥሉት ሣምንታት ይህ ተስፋፍቶ እንደሚቀጥል ይጠበቃል። ከስተቱ በሚዲያ ረገድ ያለብንን ጉድለት አጉልቶ ያሳየ በመሆኑ እያንዳንዱ ታጋይ በራሱ ጋዜጠኛ የመሆኑ ሃቅ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።

ከዓርቡ ትዕይንት በማግሥቱ ቅዳሜ የታየው የጅምላ እስር፣ ድብደባና ወከባ ደግሞ ሊቢያን የሚያስታውስ ነበር። እርግጥ ነው የፀጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ እየተደረገ ስላለው ጉዳይ ነገሬ ብሎም አልተመለከተውም። የፀጥታው ምክር ቤት ለሊቢያ የሰጠውን ትኩረት ለኢትዮጵያም ይሰጣል የሚል ብዥታ የለንም። እኛን የሚያዋጣን በገዛ ራሳችን ኃይል እና ጉልበት መተማመን እንደሆነ አሳምረን እናውቃለን። በዚህም ረገድም ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ንቅናቄዓችን አባል የሆነበት ጥምረት ለነፃነት፣ለእኩልነት (ጥምረት) እና በጄኔራል ከማል ገልቹ ከሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በጋራ ለመሥራት መስማማታቸውን የሚገልጽ የጋራ መግለጫ አውጥተዋል። ጥምረት ከሌሎችም የዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር እያደረገ ያለው ውይይት ወደ ስምምነት እየቀረበ ነው። እነዚህ ውይይቶች የትግሉ ራሱን የመከላከል አቅም ያጎለብታሉ ተብሎ ይታመናል።

ይህ የሚያሳየው ትግላችን ወደሚያደርሰን ቦታ በቆራጥነት ለመሄድ መዘጋጀታችን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም በእነዚህ ከፍተኛ መነቃቃት እያሳየ ነው። ፍርሃት ተሰብሯል። የመለስ አገዛዝ ማፈግፈግ ጀምሯል። ድልን እስክምንጨብጥ ድረስ ግን ማጥቃታችን ይቀጥላል።

ትግሉ የጠየቀንን ሁሉ ለመክፈል እኛ ዝግጁዎች ነን።

ትግላችን በሰላማዊ መንገድ እንደተጀመረ በሰላማዊ መንገድ ቢያልቅ ምኞታችን ነው። ይህ ምኞት ማሳካት የሚቻለው ግን በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ወገኖች ተገቢውን እርምጃ አሁኑኑ ከወሰዱ ነው።

1. ፍትህን፣ ነፃነትን፣ እኩልነትንና እውነተኛ ዲሞክራሲን ስትመኙ የኖራችሁ፤ ሆኖም ግን የሥራ ግዴታ ሆኖባችሁ በአገዛዙ ሠራዊት አባልነትም ሆነ በአመራር የምትገኙ ወገኖቻችን አገዛዙን በይፋ በመክዳት የሕዝብ አጋር መሆናችሁ የምታረጋግጡበት ወቅት አሁን ነው። ይህን መልካም አጋጣሚ አታሳልፉ። በመውደቅ ላይ ካለ ሥርዓት ጋር አብራችሁ አትውደቁ።
2. በተመሳሳይ ሁኔታ በጠላት የስለላ መዋቅር ውስጥ የምትገኙ ወገኖቻችንም ራሳችሁን ከአገዛዙ በይፋ የምታገሉበት ወቅት ደርሷል። ከዚህ በላይ ጠላትን ማገልገል ከቀጠላችሁ ውድ ዋጋ ያስከፍላችኋል።
3. ልቦና ያላችሁ የወያኔ፣ "አጋሬ" የሚላቸው ተለጣፊዎቹ ወይም ደግሞ ኢህአዴግ የሚባለው የይስሙላ ድርጅት አባል የሆናችሁ አሁኑኑ ከእነዚህ ድርጅቶች ለቃችሁ የሕዝብን ትግል በይፋ ተቀላቀሉ።

ይህን ዛሬ ካደረጋችሁ የበደላችሁትን ሕዝብ የመካስ እድል አላችሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብን ምህረት ብቻ ሳይሆን የድሉን ፍሬ ተቋዳሾች ትሆናላችሁ። ይህን ዛሬ ማድረግ ካልቻላችሁ ግን ነገ ልታደርጉት አይቻላችሁም። ትግላችን በየእለቱ መልኩን እየቀየረ ነው። ስለሆነም እድላችሁን አታስመልጡ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል። በጠላት ካምፕ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን እንዲቀላቀሉን ጥሪ ያደርጋል።

ግንቦት 7 መተማመናችን ኅብረታችን እና የገዛ ራሳችን ተነሳሽነት ነው ብሎ ያምናል። ሁላችንም ታጋዮች፣ ሁላችንም አርበኞች፣ ሁላችንም ዲፕሎማቶች እና ሁላችንም ጋዜጠኞች እንሁን።

አገራችንን ከዘረኛ አገዛዝ መንጋጋ መንጭቀን እናወጣታለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አሁንም ከማገገሚያ ክፍል

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

እንደሚገኙ ምንጮች ገለጹ" በሚል አርዕስት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለባቸው ከፍተኛ የሥራ ጫና ምክንያት ላጋጠማቸው ሕመም ረዘም ያለ ዕረፍት እንደሚያስፈልጋቸው ከተገለጸላቸው በኋላ ይህንኑ በውጭ አገር እየፈጸሙ እንደሆነ ታውቋል::" በማለት ዘግቧል።

በአንድ ወቅት ከበርከት ስምዖንና ከሼህ አላሙዲን ጋር በፈጠረው የጥቅም ግጭት እየተከታተለ ሲያጋልጣቸው የነበረው የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት አማረ አረጋዊ፤ የመለስ ዜናዊ ህይወት አደጋ ውስጥ መግባቱ በፈጠረበት ስጋት የባላንጣውን የበረከት ስምዖን የውሼት መግለጫ መላልሶ በማስተጋባት አንባቢዎቹን ለማደናገር እየሞከረ መሆኑ ለመታዘብ ተችሏል።

በውሸታቸው ብዛት በህዝብ ዘንድ ታአማንነት እንደሌላቸው የተረዱት የወያኔ ቁንጮዎችና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው እንደ አይናቸው ብሌን የሚሳሱለት የፖለቲካ ማህንድሳቸው አየር መተንፈሻው ተዘግቶ በተገጠመለት የአየር መተንፈሻ ቱቦ ላይ ሆኖ እያጣጣረ ባለበት በአሁኑ ሰዓት እንዴ በሰላም ወደ አዲስ አበባ ተመልሶአል ሲሉ ሌላ ጊዜ ደግሞ " ከሕመማቸው አገግመው በቅርቡ ወደ ሥራ ገበታቸው ይመለሳሉ በማለት እርስ በርሱ የተምታታ መግለጫ እየሰጡ ነው።

የወያኔ ቁንጮዎች የተምታታ መግለጫ መሳቂያ መሳለቂያ እያደረጋቸው ባለበት ሰዓት ሪፖርተር በትናትናው ዕለት ዘገባው "ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዕረፍት ጊዜያቸውን በአሜሪካ እያሳለፉ ነው ቢባልም፣ ምንጮቻችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ደኅንነት ሲባል ያሉበትን አገር ከመግለጽ ተቆጥበዋል" በማለት መዘገቡ አንባቢዎቹን የአይቶ ምስክር ድንቢጥ እንዲሉ አድርጓቸዋል።

---

## የሰሞኑ የወያኔ ባለስልጣናት ግሽበት ሃምሳ በመቶ ቀንሷል ዜማ በዓለም ታይቶና ተሰምቶ የማያቅ አሳሳች

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይህ ዲስኩር በተጨባጭ ከባዱን ኑሮን ለተሸከመው ኅብረተሰብና በተዝብት ለሚያጤነው ባለሙያ የሚቀረጠምም የሚዋጥም አይደለም። ይልቁንም መቶ ኪሎ ተሸክሞ እየተንገዳገደ ያለን ሰው አይዞህ ተቀንሶልህ ዘጠና ዘጠኝ ኪሎ ሆኖልሃል ብሎ የማሾፍ ዓይነት ነው:: በተግባር እየታየ ያለው ከአቅም በላይ የሆነ ሸክምና ከአቅም በላይ ኑሮ ነው:: ያልተኖረ ኑሮና የማይኖር ኑሮ በዝቷል በማለት እውነታውን ለማሳየት ሞክሯል::

ከዚህም ሌላ ስታትስቲክሱ ወርዶ ወርዶ ግሽበት በአገራችን አንድ መቶኛ ብቻ ቢሆንም የኑሮ ውድነት ችግር ተፈታ ማለት አይደለም:: የመግዛት አቅም በእጅጉ ተዳከሟል:: እናም መፍትሄው ከውሸት አማካሪዎችና አጎዞቻቸው መራቅ፣ብር እያተሙ ግሽበትን ከማባባስ መታቀብና የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ነው ሲል እኔ ሀላፊነቴን ተወጥቻለሁ በሚል ስሜት ገልጿል።

በመጨረሻም ጋዜጣው እየዋሹና እያለባበሱ ከመኖር እውነቱን በመናገር ትክክለኛ መፍትሄ መሻት ብቸኛው አዋጪ መንገድ መሆኑን ጠቁሟል።

## ጥምረትና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸዉን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

1. ኢትዮጵያ ዉስጥ በማዕከልም ሆነ በክልል በየትኛዉም ደረጃ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ ነፃና ፍትኃዊ ህዝባዊ ምርጫ ብቻ እንደሚሆን
2. ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚመሠረተዉ መንግስት በእዉነተኛ ፌዴራሊዝም ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን
3. የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ወቅቱና ሁኔታዉ የሚጠይቀዉን የትግል ስልት ሁሉ መጠቀም
4. የወያኔ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ አገሪቱን በግዜያዊነት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ከጋና መማር የሚገባን ቁም ነገር

ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የጋና ህዝብ የመረጣቸዉና ባለፈዉ ግንቦት ወር ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የአፍሪካን የምግብ ደህንነት በተመለከተ አሜሪካ ድረስ አስመጥተዉ ካማከሯቸዉ የአፍሪካ መሪዎች አንዱ የነበሩት ፕሬዚዳንት ጆን አታ ሚልስ በድንገተኛ ህመም ባለፈዉ ማክሰኞ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።

የጋና ዲሞክራሲ መጎልበት ምልክት እንደሆኑ የሚነገርላቸዉና የአራት አመት የስልጣን ዘመናቸዉን በቅርቡ የሚጨርሱት ፕሬዚዳንት አታ ሚልስ እንደገና ለመመረጥ በዝግጅት ላይ ነበሩ። በካካአ አምራችነቷ የምትታወቀዉ ጋና ለብዙ አመታት በመንግስት ግልበጣ፤በህዝባዊ አመጽና በፖለቲካ አለመረጋጋት ስትታመስ የከረመች አገር ነበረች። የሚያሳዝነዉ ጋና ከብዙ አመታት መራራ ትግል በኋላ በመረጠችዉ የድሞክራሲ ጎዳና ላይ በመጓዝ የምዕራብ አፍሪካ የዲሞክራሲ፤ የሠላምና የመረጋጋት ምልክት መሆኗ እየተነገራላት ባለበት ግዜ ነዉ የእድገቷና የሠላሟ ተምሳሌት የሆኑትን ታላቅ መሪዋን ያጣቸዉ።

ፕሬዚዳንት አታ ሚልስ ባለፈዉ ግንቦት ወር ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ በተካሄደዉ የአፍርካ አገሮች የምግብ ደህንነት ስብሰባ ላይ ከዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ጋር ጎን ለጎን ተቀምጠዉ መታየታቸዉ የሚዘነጋ አይደለም። ሆኖም ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ በመኪና ወደ ስብሰባዉ አዳራሽ ሲሄድም ሆነ ስብሰባዉ አዳራሽ ከገባ በኋላ ታላቅ ህዝባዊ ቁጣና ተቃዉሞ ገጥሞታል፤ ይሄዉ የህዝብ ቁጣና ተቃዉሞ አበሳጭቶት ነዉ በዚያዉ ሰሞን ከG8 ስብሰባ በኋላ ቅዳሜ ማምሻዉን ሰሜን አሜሪካ ዉስጥ የሚገኙ ቡችሎቹ ኤምባሲዉ ዉስጥ እራት ደግሰዉ ይመጣል ብለዉ ሲጠባበቁ መጣሁ ወይም ቀረሁ ሳይላቸዉ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ያቀናዉ።

የጋና ህዝብ ወድዶና ፈልጎ የመረጣቸዉ ፕሬዚዳንት አታ ሚልስ ግን "ከእንኳን ደህና መጡልን" አቀባበል ዉጭ የገጠማቸዉ ምንም አይነት ህዝባዊ ቁጣም ሆነ ተቃዉሞ አልነበረም።

በመለስ ዜናዊና በፕሬዚዳንት አታ ሚልስ መካከል ያለዉ ልዩነት በሁለቱ አገሮች ማለትም በኢትዮጵያና በጋና መካከል ያለዉ ትልቅ ልዩነት ነፅብራቅ ነዉ። ኢትዮጵያ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ነፃነት የሌለባት ዘረኝነት የነገሰባትና የሰዉ ልጆች ሰብዓዊ መብቶች የሚረገጥባት አገር ናት። ኢትዮጵያ ዉስጥ በገዢዉ ፓርቲ በህወሃት፤ በመንግስትና በአገሪቱ የኤኮኖሚ ተቋሞች መካከል ምንም ልዩነት የለም። ገዢዉ ፓርቲዉ መንግስት ነዉ ፤ ፓርቲዉ ነጋዴ ነዉ፤ ፓርቲዉ አገር አስተዳዳሪ ነዉ። በእርግጥ ጋናም የመለስ ዜናዊ አይነቱ የዘረኝነት መቅሰፍት ባይነካካትም በአንድ ወቅት ጭቆናና አለመረጋጋት የሰፈነባት የአምባገነኖች መዲና ነበረች።

ሆኖም አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚኖረዉ የጋና ህዝብ ባደረገዉ ረጂምና መራራ የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል ዛሬ ጋና የአፍሪካ የዲሞክራሲ ተምሳሌት ለመሆን በቅታለች። እንደ አዉሮፓዉያን ዘመን አቆጣጠር በ2008 ዓም በተደረገዉ የፕሬዚዳንትነት ምርጫ ፕሬዚዳንት አታ ሚልስ ያሸነፉት እጅግ በጣም ጠባብ በሆነ ዉጤት ነበር። ሆኖም የጋና ህዝብ ዉጤቱን በሠላም ተቀብሎ ወደፊት መጓዝ በመቻሉ አለም የጋናን ህዝብ በሳልነትና አገሪቱ በአጭር ግዜ ዉስጥ የገነባቻቸዉን የዲሞክራሲ ተቋሞች ብቃት አድንቋል።

በአንፃሩ ለጋና ህዝብ ነፃነት ቁልፍ ሚና የተጫወተችዉ አገራችን ኢትዮጵያ ግን ዛሬ ዘረኝነት የነገሰበት፡ የህዝብ መብት የሚረገጥባትና የአፍሪካ የአፈና፤ የእስር፤የስደትና የሰቆቃ ቋሚ ምልክት ሆናለች። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በዲሞክራሲ ስም የዲሞክራሲ መብቶች የሚረገጡባትና የሚጨፈለቁባት አገር ናት።በአጠቃላይ ዛሬ የምንኖርበት ግዜ የመረጃ ዘመን ተብሎ በሚጠራበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የገዛ አገሩን ሁኔታና የግል ህይወቱን ጭምር በተለመለከተ ምንም አይነት መረጃ እንዳያገኝ ተደርጎ በጨለማ ዉስጥ የሚኖር ህዝብ ሆኗል።

የጋና ህገ መንግስት ፕሬዚዳንቱ በጤና መታወክ ወይም በሌላ ምክንያት ስራዉን መስራት ካልቻለ ማን ተክቶት እንደሚሰራና አገሪቱን እንደሚመራ በግልጽና በማያሻማ መልኩ ያስቀመጠዉ ስለሆነ ፕሬዚዳንቱ ባለፈዉ ማክሰኞ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጆን ማሃማ ቃለ መኃላ ፈጽመዉ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሆነዋል። በፕሬዚዳንቱ ድንገተኛ ሞት የጋና ህዝብ ታላቅ ኃዘን የተሰማዉ ቢሆንም - ደሞ "ማን ይመጣብን ይሆን" እያለ ግራ አልተጋባም። ጋና ዉስጥ ህዝብ የመረጃ ባለቤት ስለሆነ ፕሬዚዳንት አታ ሚልስ ታመዉ በቆዩበት የአንድ ቀን ግዜ ዉስጥም ቢሆን የፕሬዚዳንቱ መታመም በሚስጢር አልታየዘም።

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን መሪ ነኝ ተብዬዉ መለስ ዜናዊ ታምሞ ዉጭ አገር ሄዶ መታከም ከጀመረ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ነዉ የዚህ ዘረኛ ሰዉ መታመም በይፋ ለህዝብ የተነገረዉ። እዚህ ላይ አንድ የሚያሳዝንንና የሚገርመን ነገር ቢኖር ኢትዮጵያን እመራለሁ የሚለዉን ሰዉ መታመም ኢትዮጵያዉያን ለመጀመሪያ ግዜ በአደባባይ የሰሙት ከሌላ የአፍሪካ አገር መሪ ነዉ። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት በግልጽ ያላስቀመጠዉና ዛሬ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ እያወዛገበ ያለዉ ጉዳይ መለስ ዜናዊ የመጨረሻ ትንፋሹን ቢተነፍስ ማን ይተካዋል የሚለዉ ጥያቄ ነዉ። መለስ ዜናዊ ህግ መንግስቱን ሲጽፍ እራሱን እንደ መጀመሪያና እንደመጨረሻ አድርጎ ስላየ ይህንን አስፈላጊ የሆነ የአገር ጉዳይ ሆን ብሎ ዘልሎታል። እንግዲህ የጋናና ኢትዮጵያ ልዩነት ይህንን ያክል የሰፋ ነዉ። እዚህ ላይ አንድ ነገር መልሶ መላልሶ ወለል ብሎ ሊታየን ይገባል፡ የጋና ህዝብ በአጭር ግዜ ዉስጥ እዚህ የሚያስቀና ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለዉ አምርሮ ጨቋኝ መሪዎቹንና ስርአታቸዉን ስለታገለ ነዉና እኛም እነዚህ ዛሬ ተመቻችተዉ የምናያቸዉ ሁኔታዎች ሳያመልጡን የዘረኞችን ስርአት በአንድነት ተነስተን ነገ ሳይሆን ዛሬ መደምሰስ አለብን።

## የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ለሐይማኖት ነፃነትና ለሰብአዊ መብቶች መከበር

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ላይ ሠልፈኛዉ እጅ ለእጅ ተያይዞ ካሰማቸዉ የተለያዩ "መብታችን ይከበር" ከሚሉ መፈክሮችና መዝሙሮች ዉጭ ሌላ ምንም አይነት መረን የለቀቀ አካሄድ አልታየበትም። በብዙ የአለማችን አካባቢዎች የተካሄዱትን ሠላማዊ ሠልፎች የተከታታሉ የዲፕሎማቲክ ምንጮች የአዲስ አበባዉ ሰልፍ እንኳን መሳሪያ የታጠቀ ሀይል ተራ ጠባቂም የሚያስፈልገዉ እንዳልነበረ በግልጽ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በማግስቱ ቅዳሜ ዕለት የተካሄደዉ ሠላማዊ ሠልፍ ጅምሩ እንደ ዕለተ አርቡ ሠልፍ ሠላማዊ የነበረ ቢሆንም የሠላም ፀር የሆነዉ የወያኔ አገዛዝ ያሰማራቸዉ ፖሊሶችና የፀጥታ ሀይሎች በወሰዱት ፀረ ህዝብና ፀረ መብት እርምጃ ከፊል አዲስ አበባ ሲተራመስ ዉሏል። የፌደራል ፖሊስና የወያኔ ልዩ የፀጥታ ሀይሎች የታላቁን አንዋር መስጊድ ግቢ ጥሰዉ በመግባት ህዝበ ሙስሊሙን በቆመጥና በሠደፍ ከመደብደባቸዉም በላይ ምዕመኑ ፈጣሪዉን በሚያመልክበት የተቀደሰ ቦታ ላይ የጋዝ ጭስ በመርጨት እጅግ በጣም አረመኔያዊ የሆነ ግፍና በደል ፈጽመዋል። አርብ ሐምሌ 13 ቀን በተካሄደዉ ሠላማዊ ሠልፍ ፀጥ ብለዉ የዋሉት ከአንዋር መስጊድ እስከ ሰባተኛ ያሉት ቦታዎችና እንዲሁም የተከለሐይማኖት አካባቢዎች የአገዛዙ ታጣቂዎች በከፈቱት ተኩስ የጦርነት ወረዳ መስለዉ ዉሏል። ወያኔ የሙሲሊሙን ሰላማዊና ህጋዊ ጥያቄ በሃይል ለመደፍጠጥ ሲል በወሰደዉ አረመኔያዊ እርምጃ የፖሊስና የሲቪል ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች ሰላማዊ ዜጎችን በቆመጥ ዱላ በጭካኔ ሲቀጠቅጡዋቸው የተቀረጸ ቪዲዮ በድረገጽ አማካኝነት ተሰራጭቶ የብዙሃንን ቁጣ የቀሰቀሰ ሲሆን እስከዛሬ በአገራችን ይደረግ የነበረውን ግፍና መከራ በምን ቸገረኝነት ከዳር ሆነው ይመለከቱ የነበሩትን ሳይቀር በማስቆጣት ለትግል እንዲነሳሱ አድርጎአል።

የወያኔው አገዛዝ ይህንን ጨካኝና የአፈና እርምጃውን ለማድበስበስ በመሞከር በሚቆጣጠራቸዉ የዜና ማሰራጫ አዉታሮች "መንግስት በወሰደዉ በሳል እርምጃ የፀረ ሠላም ሀይሎችን ተቃዉሞ በቀላሉ ለመቆጣጠር ችሏል" እያለ በተለመደ የማደናገሪያ ስልቱ ህዝብ እያደናቆረ ይገኛል።

ሆኖም በፀረ ሠላምነት ተፈርጀዉ መታሰር ያለባቸዉ የወያኔ መሪዎች እንጂ መብታቸዉን የጠየቁ ሠላማዊ ሠልፈኞች አለመሆናቸዉንና በበሳልነቱና በአርቆ አስተዋይነቱም መወደስ ያለበት ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ሳይሆን ህዝበ ሙስሊሙ መሆኑን አርብና ቅዳሜ ዕለት የተካሄዱት ሠላማዊ ሠልፎች በግልጽ አሳይተዋል የሚል የፖለቲካ ትንታኔ ከአዲስ አበባና ጉዳዩን በቅርብ ከሚከታተሉ የዉጭ ወገኖችም ተደምጧል።

## ጥምረትና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸዉን

. . . (ከገፅ 2 የዞረ)

የሚያስተዳድር ከሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና የሲቪክ ድርጅቶች የተዉጣጣ የሽግግር መንግስት መመስረት

5. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ጉዳዮችና ክንውኖች ሁሉ ተግባራዊ የሚሆኑት ኢትዮጵያ ተብላ በምትጠራዉ ሉዓላዊ አገር ዉስጥ እንደሚሆኑ ናቸው።

በመጨረሻም በመንገዳገድ ላይ የሚገኘዉን ዘረኛ የወያኔ ስርዐት በተባበረ ህዝባዊ ሀይል ገፍቶ መጣልና በምትኩም ለዜጎች በነ ፈቃድ የሚገዛና ዜጎችን በእኩልነት የሚመለከት ዲሞክራሲያዊ ስርዐት መመስረት የዚህ ትዉልድ ታሪካዊ ሐላፊነት መሆኑን አጥብቆ ያሰመረዉ የአነግና የጥምረት መግለጫ ለኢትዮጵያ ህዝብ "ተነስ" የሚል የትግል ጥሪ በማስተላለፍ ተጠናቅቋል።

**ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነት (ምረት)**

**እና**

**ለፍትህ በኢትዮጵያና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)**

**የጋራ መግለጫ**

**ሐምሌ 12 ቀን 2004**

የወያኔ ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ስልጣን ይዞ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ዉስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ከጠየቃቸዉ ጥያቄዎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የተቃዋሚ ኃይሎች የትብብር ጥያቄ ነዉ። ይህ እልህ አስጨራሽ የሆነዉ የጋራ ትግል ጥያቄ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ለረጂም ግዜ መልስ ሳያገኝ ቆይቷል። ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከደረሰበት የእድገት ደረጃና አገራችን ከምትገኝበት ሁኔታ አኳያ የጋራ ትግል አማራጭ የሌለዉ ብቸኛ መንገድ በመሆኑ በቅርቡ አመርቂ የሆኑ የትብብርና አብሮ የመሥሥራት መልካም ጅምሮች እየታዩ ነዉ። ከእነዚህ የትብብር ጅምሮች ዉስጥ አንዱ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርና ጥምረት ለነፃነት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ *(ጥምረት)* በተከታታይ ያካሄዱትና በየደረጃዉ ለሕዝብ ያስተዋወቁት የትብብር ጥንስስ ነዉ።

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባርና ጥምረት ለነፃነት፣ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ (*ጥምረት*) ከፍተኛ አመራሮች ባለፉት ጥቂት ወራት ባካሄዱት ቀጣይና ተከታታይ የጋራ ስብሰባዎች የወያኔን ሥርዓት ለማስወገድና ሁሉን አቀፍ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ ናቸዉ ብለዉ ባመኑባቸዉ በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

1. በአንድ ላይ የመሰባሰብና በጋራ የመታገል ዓላማና ፍላጎት ያላቸዉን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ያካተተ ሰፋ ያለ ግንባር እንዲፈጠርና በፍጥነት ሁለ-ገብ የትግል እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ጥምረትና ኦነግ የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።
2. ይህ ብዙ የፖለቲካ ኃይሎችን የሚያካትት ሰፊ ግንባር እስኪመሠረት ድረስ ባለዉ ግዜ ጥምረትና ኦነግ ድርጅታዊ ብቃታቸዉን አቀናጅተዉ የፖለቲካ *ሥራዎችን፤* የዉጭ ግኑኝነት *ሥራዎችን፤*የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ *ሥራዎችን፤* አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚደረጉ ድርጅታዊና ሌሎችም የትግል እንቅስቃሴዎችን በጋራ አቀናጅተው ለመሥራት ተስማምተዋል።

ጥምረትና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አስከዛሬ ባደረጓቸዉ የጋራ እንቅስቃሴዎችም ሆነ ለወደፊት በሚያደርጉት የጋራ ትግል ከዚህ ቀደም ለሕዝብ በይፋ ቃል የገቡትንና ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና የትግል መርሆዎችና ግቦች የወያኔ አገዝዝ እስከተወገደና በምትኩ ሁሉን አቀፍ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እስኪመሠረት ድረስ የሚገፉባቸዉ ሆናቸዉን በአጽንኦት በድጋሚ ቃል ገብተዋል።

1. ኢትዮጵያ ዉስጥ በማዕከልም ሆነ በክልል በየትኛዉም ደረጃ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ ነፃና ፍትኃዊ ህዝባዊ ምርጫ ብቻ እንደሚሆን፤
2. ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚመሠረተዉ መንግስት በእዉነተኛ ፌዴራሊዝም ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን፤
3. የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ወቅቱና ሁኔታዉ የሚጠይቀዉን የትግል ስልት ሁሉ መጠቀም፤
4. የወያኔ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ አገሪቱን በግዜያዊነት የሚያስተዳድር ከሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና የሲቪክ ድርጅቶች የተዉጣጣ የሽግግር መንግስት መመስረት፤

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ጉዳዮችና ክንውኖች ሁሉ ተግባሪዊ የሚሆኑት ኢትዮጵያ ተብላ በምትጠራዉ ሉዓላዊ አገር ዉስጥ እንደሚሆኑ ናቸው።

የራሱ ክፋትና ተንኮል ጠላልፎት ወደማይቀርለት መቃብሩ እየወረደ ያለዉን የወያኔ ዘረኛ ስርዓት በጋራ ህዝባዊ ኃይል በመግፋት ግብአተ መሬቱን ማፋጠን ከዚህ ትዉልድ የሚጠበቅ ታሪካዊ ግዴታ ነዉ። ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ ጥምረትና ኦነግ ለሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና ትግሉ በቀጥታ ለሚመለከተዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአብረን እንታገል ሀገራዊ ጥሪያቸዉን ያስተላልፋሉ።

በተባበረ የሕዝብ ትግል ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

# የዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ጤንነት ጉዳይ አሁንም በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን እያነጋገረ ነው

ዋሺንግተን ዲሲ ሮናልድ ሬገን ህንፃ ዉስጥ እንደ ጥይት የተወረወረበት የጋዜጠኛ አበበ ገላዉ ድምጽ ከፉኛ ካስደነገጠዉ በሁዋላ ቆሌ ርቆት ከፖለቲካ አደባባዮች ሁሉ ጭልጥ ብሎ የጠፋዉና በቤልጅዬም ዋና ከተማ ብራሰልስ ዉስጥ ህክምና ላይ የሚገኘዉ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ አገዛዙ ለህዝብ በሚሰጠዉ የተምታታ ዜናና የዲፕሎማሲ ምንጮች በሚሰጡት መግለጫ ታጅቦ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብንም ሆነ በአገራችን ያሉትን የዲፒሎማቲክ ማህበረሰብ በከፍተኛ ደረጃ እያነጋገረ መሆኑ ታውቆአል።

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የስርዐቱ ቁንጮ የሆነዉን የመለስ ዜናዊን በጸና መታመም ለመደበቅ ቢሞክርም ነገሩ "ግመል ሰርቀህ አጎንብስ" ነዉና የኢትዮጵያ ህዝብ የመለስ ዜናዊን መታመም ብቻ ሳይሆን የበሽታዉን አደገኛነትና ዬት አገር በህክምና ላይ እንደሚገኝ ጭምር ጠንቅቆ ካወቀ ሳምንታት ተቆጥረዋል። ተንኮላቸውንም ሆነ ድብቅ ሴራቸውን በድብብቆሽ ላይ የተመሠረተዉ የወያኔ መሪዎች የመለስ ዜናዊን ህመም " ከስራ ብዛት የመጣ ድካም ነዉ ፤ በቅርቡ አገግሞ ወደ መደበኛ ስራዉ ይመለሳል" እያሉ ቢቀባጥሩም ታማኝ ምንጮች መለስ ዜናዊን የለከፈዉ በሽታ እንዲህ በቀላሉ የማይገላገሉት በሽታ መሆኑን ተናግረዋል። ታዋቂ የሆኑ የተለያዩ አለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን የዲፕሎማቲክ ምንጮቻቸውን በመጥቀስ መለስ ዜናዊ ከሞት ጋር እየተፋጠጠ ነው ሲሉ መዘገባቸው ይታወሳል።

በአንጻሩ በወያኔ ቁጥጥር ሥር ያሉ አንዳንድ ሚዲያዎች ከአለቆቻቸው የሚሰጠውን የተሳሳተ ዜና በማራገብ መለስ ዜናዊ በቅርቡ ተሽሎት ወደሥራው ይመለሳል በማለት ህዝብ የማደናገር ስልታቸውን ተያይዘውታል። ባለፈዉ አርብ ሐምሌ 13 ቀን ለህዝብ እይታ የበቃዉ የዋልታ እንፎርሜሺን ማዕከል መለስ ዜናዊ በመልካም ጤንነት ላይ እንደሚገኝና በቅርቡም ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመለስ ሲገልጽ ፎርቹንና ኢትዮጵያ ፈርስት የተባሉ ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸዉ ጋዜጦች ደግሞ መለስ ዜናዊ በዚያኑ ዕለት ማለትም አርብ ሐምሌ 13 ቀን አዲስ አበባ ገብቶ ማደሩን ዘግበዋል።

የዘረኛው መለስ ዜናዊን ጤንነት በፈጠረው ስጋት የህወሃት አመራሮች በከፍተኛ የሥልጣን ሹኩቻ ውስጥ መግባታቸው የአደባባይ ምስጥር ሆኖ እያለ፤ አለቃቸው በቶሎ ወደሥራ ይመለሳል በማለት ለህዝብ የሚሰጠው የማደናገሪያ መግለጫዎች ማንንም እንዳላሳመነ ከአገር ቤት የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ህወሃቶች መለስ ዜናዊን ለአንዴና ለመጨረሻ እንደተነጠቁ እያወቁ የሚሰጡት እርስ በርሱ የተምታታ መግለጫዎች በመላው አገሪቱ እየተቀጣጠለ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞ ለመረጋጋት ፋታ እንዳይነሳቸው ከመስጋት የመነጨ ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው።

ወያኔ መካከል በተጀመረው ከፍተኛ የሥልጣን ፋክክር ስዩም መስፍን ከቻይና መጥቶ በማረጋጋት ሥራ ተጠምዶ በሚገኝበት በአሁኑ ሰዓት የይስሙላ ጠቅላይ ሚንስቴር የተባለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ሌላኛው አለቃው ስይሙ መስፍን ትቶት ወደመጣበት ቻይና ለሥራ ጉብኝት በሚል ሸፋን መላኩ ከህወሃቶች በበስተቀር ሌሎች ከጫወታው ውጪ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው ተብሎአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>**ማሳሰቢያ**</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org